


## የአጠቃላይ እቅድ ማሻሻያ ፕሮጀክት፡ የአርሊንግተን ረቂቅ መመሪያ መርሆዎች

ዛሬ ስለ አርሊንግተን ረቂቅ መመሪያ መርሆዎች በሰባት ክፍሎች የሚቀርብ ተከታታይ መረጃ ማጋራት እንጀምራለን፤ የመጀመሪያውም ***በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ዘርፍ የሚበለጽግ አርሊንግተን*** የሚለው ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ መመሪያ መርሆ በማሕበረሰቡ አስተያየት፣ እንዲሁም ካውንቲው ቀድሞ ባጸደቃቸው ፖሊሲዎችና ተነሳሽነቶች ላይ ተመርኩዘው የተቀረጹ ደጋፊ መግለጫዎችን አካቷል፡፡

## *መመሪያ መርሆዎች ምንድን ናቸው?*

እነዚህ አጠቃላይ ዕቅዱ በከፍተኛና ሁሉን አቀፍ ደረጃ ሊከተለው የሚገባውን አቅጣጫ የሚገልጹ በእሴት ላይ የተመሰረቱ መግለጫዎች ሲሆኑ እቅዱ የሚያካትታቸውን ግቦች፣ ፖሊሲዎች፣ ካርታዎችና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ይመራሉ፡፡

## *ደጋፊ መግለጫዎች ምንድን ናቸው?*

እነዚህ የፖሊሲ አቅጣጫን የሚጠቁሙና ለእያንዳንዱ መመሪያ መርሆ ሰፋ ያለ ማብራሪያና ትርጓሜ የሚሰጡ ገላጭ መግለጫዎች ናቸው፡፡

*መመሪያ መርሆዎቹና ደጋፊ መግለጫዎቹ የሚጣጣሙባቸውን በካውንቲው የጸደቁ ፖሊሲዎችና ተነሳሽነቶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማንበብ የፕሮጀክቱን ሰነዶች ድረገጽ ይጎብኙ፡፡*




## . የአርሊንግተን ካውንቲ መሪ መርህ፡ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ረገድ ጸኑ የሆነ አርሊንግተን

**መሪ መርህ መግለጫ፡ አርሊንግተን አዳዲስ ፈጠራዎችን ያከለና የገበያ ለውጦችን ያገናዘበ እድገትን በማበረታታት፣ የተለያዩ የንግድ ዘርፎችን በመደገፍ እንዲሁም አስፈላጊ አገልግሎቶችና መገልገያዎች በፍትሃዊነት እንዲገኙ በማድረግ የኢኮኖሚ ጥንካሬንና የማህበረሰብ ብልጽግናን እንደምታጎለብት ማረጋገጥ፡፡**

## ደጋፊ መግለጫዎች፡

**ከእሴት ጋር የተጣጣመ እና በፋይናንስ ረገድ ኃላፊነት የተሞላበት እድገት፡** የሕዝብ ሀብትን ጥራትና ኃላፊነት የተሞላበት አያያዝን በመጠበቅ የጸደቁ እቅዶችንና ፖሊሲዎችን የሚያንፀባርቁ እንዲሁም የማህበረሰቡን እሴቶችና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች የሚያራምዱ የመንግስትና የግል ኢንቨስትመንቶችን መምራት፡፡

**የኢኮኖሚ ብዝሃነትና ኢንቨስትመንት፡** የንግድ ኢንቨስትመንትን፣ ቆይታንና መስፋፋትን የሚደግፍ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ጥንካሬንና ብዝሃነትን ማጎልበት፤ እንዲሁም በስነጥበብ፣ በባህል፣ በቱሪዝምና ማህበረሰቡን በሚያገለግሉ ተቋማት ላይ የተመሰረቱ የበለጸገ የተቀላቀሉ አገልግሎት ቦታዎችን ማበረታታት።

**አካታች ስራ ፈጠራና የንግድ ስነምህዳር፡** አነስተኛ ንግዶች እንዲበለጽጉ ወደ ዘርፉ ለመግባትና ለማደግ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን በመቀነስ እንዲሁም አዳዲስ ትስስሮችንና እድሎችን በማቅረብ አካታች የስራ ፈጠራንና የአነስተኛ ንግዶችን ስኬት ማስቻል።

**ተለዋዋጭነትና የንግድ ዘርፍ ጥንካሬ፡** የንግድ መስመሮችን ህያውነትና ጥንካሬ የሚደግፉ፣ እንዲሁም ነባር ቦታዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ማዋልን የሚያበረታቱ ተለዋዋጭና የገበያ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲዎችንና ደንቦችን በመተግበር ተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታዎችን መቋቋም ማስቻል።

**የስራ እድልና የኢኮኖሚ እድገት፡** እየተለወጡ ባሉ ኢንዱስትሪዎችና ቴክኖሎጂዎች ውስጥ ካሉ የስራ ዘርፎችና ክህሎቶች ጋር የሚጣጣሙ የእድሜ ልክ ትምህርትና የስልጠና እድሎችን በማመቻቸት የኢኮኖሚ እድገትን ማሳደግና የክህሎት ምንጮችን ማጠናከር።

**የቤተሰብ መረጋጋትና ሀብት ማፍራት፡** የቤተሰብን መረጋጋት የሚያጠናክሩ፣ ሀብት ማፍራትን የሚያስችሉ፣ የቤት ባለቤት የመሆን መንገዶችን የሚያሻሽሉና ወደ ስራ ዓለም ለመግባት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን የሚቀንሱ እቅዶችን፣ ፖሊሲዎችንና ተደራሽ ድጋፊ አገልግሎቶችን ማበረታታት።

**ማህበራዊ መሠረተ ልማትና ዝግጁነት፡** በጠንካራ ማህበራዊ መሠረተ ልማት፣ በአየር ንብረት መቋቋም፣ በአደጋ ጊዜ ዝግጁነትና በአስተማማኝ መሠረታዊ አገልግሎቶች አማካኝነት የሰዎችን ኑሮና ደህንነት መጠበቅ እንዲሁም የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ኪሳራንና የአገልግሎት መቋረጥን መከላከል።

---

## የእርስዎን አስተያየት እንፈልጋለን!

የማሕበረሰቡ አባላት የኖሩበት ተሞክሮ፣ ፍላጎቶችና እሴቶች በአጠቃላይ ዕቅዱ መግቢያ ላይ እንዲንጸባረቁ በእነዚህ የአርሊንግተን ረቂቅ መመሪያ መርሆዎችና ደጋፊ መግለጫዎች ላይ የሚሰጥ የማኅበረሰብ አስተያየት እጅግ አስፈላጊ ነው።

[የእርስዎን አስተያየት እዚህ ያጋሩ።]

***እባክዎን እስከ እሁድ ጁን 7 ድረስ አስተያየትዎን ይስጡ።***

## ተጋብዘዋል!

የበለጠ ለመረዳትና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ **በስራ ሰዓት** ቢሯችን ብቅ ይበሉ ወይም **የሕዝብ ግንኙነት መርሃ ግብሮቻችን ላይ ይጎብኙን**!

<u>የቢሮ የስራ ሰዓታት</u>

- ሐሙስ ሜይ 21፣ ከ 12-2 ፒ.ኤም.፣ ፌርሊንግተን የማሕበረሰብ ማእከል ክፍል ቁጥር 118
- ሐሙስ ሜይ 21፣ ከ 6-8 ፒ.ኤም.፣ ፌርሊንግተን የማሕበረሰብ ማእከል ክፍል ቁጥር 118
- ማክሰኞ ጁን 2፣ ከ 12–2 ፒ.ኤም.፣ ሄንድሪ ሃውስ
- ማክሰኞ ጁን 2፣ ከም 6–8 ፒ.ኤም.፣ ሄንድሪ ሃውስ

<u>የሕዝብ ግንኙነት መርሃ ግብሮቻችን</u>

- ዓርብ ሜይ 15፣ በብስክሌት ወደ ስራ የሚሄዱበት ቀን፣ ሮዝሊን መቆሚያ ፣ 7–9 ኤ.ኤም
- ቅዳሜ ሜይ 16፣ የኮርትሃውስ ገበሬዎች ገበያ፣ 8 ኤ.ኤም.–12 ፒ.ኤም.
- እሁድ ሜይ 17፣ የዌስቶቨር ገበሬዎች ገበያ፣ 8 ኤ.ኤም.–12 ፒ.ኤም.
- ቅዳሜ ሜይ 30፣ የሜትፓርክ ገበሬዎች ገበያ፣ 9 ኤ.ኤም.–1 ፒ.ኤም.
- እሁድ ሜይ 31፣ የኮሎምቢያ ፓይክ ገበሬዎች ገበያ፣ 9 ኤ.ኤም.–1 ፒ.ኤም.